# እፎዬው ግልግል አንድ ዕዳ ቀለለ

አገሬ ከስዊድን
ነሀሴ 2012

እፎዬው ግልግል፤ ክብር ለፈጣሪ
መልስ እያገኘ ነው፤ የህዝብ የእንባ ጥሪ
እፎየው ግልግል፤አንድ እዳ ቀለለ
ሞትም ያስደስታል፤ግፈኛ ከጣለ

የትግራይ ተወካይ ፤የኢትዮጵያ ጠላት
በሰቆቃ ገዝቶ ፤ለ21 አመት
ጉድጓድ እየማሰ ፤ኢትዮጵያን ሊቀብራት
ጅምሩን ሳይጨርስ ፤ህልሙ ሳይሳካ
ሞት ነጥቆ ወሰደው ፤ይህም አለ ለካ!

መለስ ብለን እንይ ፤ቀድመን ባለፍንበት
በመሰሪ ጓዱ ፤በተንኮል በረከት
በዘረኛ ትምሕርት ፤ክፋተ ስብሀት
አፈር እያስበላ ፤ሲያሰቃየን ኑሮ
አምላክ ሰማውና ፤የህዝቡን ሮሮ
እሱም አልቀረለት ፤ተቀጨ ዘንድሮ ።

ልብ ያለው ልብ ይበል ፤ጎጠኛ ዘረኛ
በዘር የሚያሰቃይ ፤ለህዝብ የማይተኛ
ይጠፋል የወድቃል ፤ተጠልቶ ተንቆ
የሚያዝን ልብ የለም ፤አስከሬኑ ወድቆ ።

ህዝብ ሲፈራቸው ፤ ሲገሉና ሲያስሩ
ለካስ ፍርሀት ሆኖ ፤የጭካኔው ስሩ
እንደደነገጠ ፤በአለም አደባባይ
መለስ ተሰወረ ፤መልሶ እንዳይታይ ።

የምስራች ወገን ፤የኖርክ በጭቆና
የድል ዋዜማ ነው ፤የሰማነው ዜና
ስንቱን ሰው ወንጅሎ ፤የሞት ፍርድ ፈርዶ
ፍርደ ገምድሉ ሰው ፤በአምላክ ተወግዶ
ቀድሟቸው አለፈ ፤ደረሳቸው መርዶ ።

ተሸጠን ተሰደን ፤ተግዘን ተገፍተን
አሸማቆ ይዞን ፤ሳለን አንገት ደፍተን
የላይኛው ጌታ ፤አይቶ ተመልክቶ
ፍርዱን ፈረደና ፤እኛም አየን ሞቶ ።

እግዚአብሔር ይመስገን ፤ሁሉም አለው ተራ
ፊትህን መለስከልን ፤ሲበዛ መከራ
ተንኮልን ሾራቢ ፤የሀገር ቀበኛ
አለ በጫንቃችን ፤ብዙ ወንጀለኛ
ፍርድን ጀምረሀል ፤ከቁንጮ ከአናቱ
የኢትዮጵያ ህዝብ እንባ ፤አልቀረም በከንቱ
ሁሉንም ገላግለን ፤አምላክ ሆይ አቤቱ ።

ትንፋሽ ስላገኘን ፤አንድ መኻርገር ነቅለህ
ጎስቋላ ህዝብ አለ ፤ተመስገን የሚልህ
ጨርሰህ ገላግለን ፤በጀመረው እጅህ
በመለስም መሞት ፤ ሀዘን ለገባቸው
እንዳይለያዩ ፤እዚያው ሰብስባቸው ።